የኮሎምቢያ ዲስትሪክት
የግዛቱ የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ ለ
ትምህርት

ዉድ ወላጆች፣

በሳለፍነዉ የጸደይ ወራት፣የእርስዋ ልጅ አዲስ በሆነዉ የፓርትነርሺፕ ፎር አሴስመንት ኦፍ ሬዲነስ ፎር ኮሌጅ ኤንድ ኬሪየርስ(ፒኤአርሲሰ(PARCC)) የእንግሊዘኛ ቋንቋ ጥበብ እና ሂሳብ ትምህርት ዘርፎች ግምገማ ላይ ተሳታፊ እንደነበር/ች ይታወሳል፡፡ አዲሱ ግምገማ፣ የዲሲ ሲኤኤስ(DC CAS) በንባብ፣በማቀናበር እና በሂሳብ ትምህርት ዘርፎች ግምገማን የሚተካ ሲሆን፣በይዘቱ ጠንከር ያለ እና የተማሪዋችን የትምህርት ሂደት በጉልህ የሚያሳይ ግምገማ ነዉ፡፡

የእርስዋ ልጅ ዉጤት፣እንዲሁም የትምህር ቤቱ እና የወረዳዉ አማካይ ዉጤት፣በአሁኑ ዓመት የተለየ ሆኖ ሊመጣ ይችላል፡፡ይህ ደግሞ የሚሆንበት ምክንያት አዲሱ ፈተና ከበፊቱ በበለጠ ዉስብስ፣በዓለም ዙሪያ ስራ ላይ የሚዉሉ ክህሎቶችን፤በሳል አስተሳሰብ፣ጽሁፍ፣እና ችግር ፈቺነትን የሚለካ ግምገማ ስለሆነ ነዉ፡፡ሆኖም ግን በዲሲ ሲኤኤስ(DC CAS) ላይ ከጊዜ ጋር ለዉጦችን ማየት እንደቻል ነዉ ሁሉ፣የእኛ የዚህ ግምገማ ዉጤትም በቀጣዩቹ ዓመታት እየተሻሻለ እንደሚመጣ ሙሉ እምነት አለን፡፡

መስፈርት የወጣላቸዉ ፈተናዋች ዉጤት የተማሪዋችን አንድ የተነጠለ የትምህርት ሂደትን ብቻ እንደሚለኩ ማስታወስ እጅግ ጠቃሚ ነዉ፡፡ ከሌሎች መለኪያዎች ጋር በሚቀናጁበት ጊዜ፤ማለትም በአስተማሪ እይታ እና በከፍል ስራዋች ሲደገፍ፣የፒኤአርሲሰ(PARCC) ፈተና የተማሪዋችን አጠቃላይ የትምህርት ብቃት ያሳያል፡፡

የእኛ የመጨረሻዉ አላማችን ሁሉም ተማሪዋች በኮሌጅ እና ከዛም በሁዋላ ባለዉ ህይወታቸዉ ዉጤታማ መሆን እንዲችሉ ሆነዉ መቀረጻቸዉን እና በአሁኑ የትምህርት ዓመት ላይ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ትኩረት ሆነዉ መቀጠላቸዉን ማረጋገጥ ነዉ፡፡

ግዛቱ አስተማሪዋችን እና ተማሪዋችን እንዴት እየደገፈ እንደሆነ ወደ እናንተ መረጃ ለማድረስ ጠንክረን የምንሰራ ይሆናል፤እንዲሁም በትምህርት ዓመቱ ዉስጥ የዉይይት እና አስተያየት የመስጫ እድሎችንም የምናመቻች ይሆናል፡፡

በዲሴምበር ወር ዉስጥ፣የእርስዋ ልጅ ፓርትነርሺፕ ፎር አሴስመንት ኦፍ ሬዲነስ ፎር ኮሌጅ ኤንድ ኬሪየርስ(ፒኤአርሲሰ(PARCC)) ግምገማ ዉጤት ይደርሶታል፡፡ለእንግሊዘኛ ቋንቋ ጥበብ ራሱን የቻለ ሪፓርት እና ለሂሳብ ትምህርትም ሌላ ሪፓርት ይደርሶታል፡፡

የእርስዋ ልጅ በቀጣዩ የትምህርት ዓመት ላይ የእርሱን/ሷን ብቃት ለማሻሻል እርስዋ ሊጠቀሙ የሚችሉዋቸዉን አቅርቦቶችን ከማቅረብ በተጨማሪ፤ይህ መመሪያ ከእርስዋ ልጅ የዉጤት ሪፓረት ሊገነዘቡ ወደሚችሉዋቸዉ 5 ዋና ዋና ነገሮች ይመራዋታል፡፡

አጠቃላይ የሆነ ጥያቄ ካልዋት ወይም ስለግምገማዋቹ የበለጠ መረጃ ከፈለጉ፣እባክዋትን የእኛን ድህረ ገጽ ይጎብኙ http://osse.dc.gov/parcc.

ከምስጋና ጋር፣

ሀንሱል ካንግ
የበላይ ተቆጣጣሪ




## 2) የእርስዎ ተማሪ ምን ያህል ልዩ የሆነ እዉቀት እና ክህሎቶችን አዳብሯል/ለች?

ተማሪዎች ስለ ጥንካሬያቸዉ እና ተጨማሪ ድጋፍ በሚያስፈልጋቸዉ ሁኔታዎች ላይ ጥልቅ የሆነ መረጃን በብዙ ንዑስ-ምድቦች ያገኛሉ፡፡ምንም እንኳን የቁጥር ዉጤቶች ለንዑስ-ምድቦች የሚሰጥ ባይሆንም፣ሪፓርቱ ተማሪዎች የሚጠበቀዉን ወይም ከሚጠበቀዉ በላይ ዉጤት ማምጣታቸዉን፣ወይም የሚጠበቀዉን ዉጤት ለማስመዝገብ ጥቂት እንደሚቀራቸዉ ወይም ከሚጠበቀዉ በታች ዉጤት ማምጣታቸዉን ያሳያል፡፡

## 3) እርሱ ወይመ እርሷ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ሲወዳደር ዉጤቱ ምን ያህል ነዉ?

ሪፓርቱ የእርስዋ ተማሪ ዉጤት ከእርሱ/ሷ ያለፋ የዲሲ ሲኤኤስ(DC CAS) ፈተና ዉጤቶች ጋር ተያያዝነት እንዳለዉ እና ከባለፈዉ ዓመት ዉጤት ጋር ሲወዳደር ልጅዎ ከእርሱ/ሷ እኩዬች ጋር ሲነጻጸር የትኛዉ ትምህርት ዘርፍ ላይ ስኬታማ መሆን እንዳልቻለ/ለች ያሳያል፡፡

## 4) ከዚህ በፊት ከነበሩት ዉጤቶች ጋር የአሁኑ የልጁ ዉጤቶች እንዴት ይነጻጸራሉ?

የፒኤአርሲሲ(PARCC) ግምገማዎች አዲስ መለኪያ መስመርን የሚያስቀምጡ ሲሆኑ፤የልጅዎ የፈተና ዉጤቶች ከእርሱ/ሷ ያለፋ የዲሲ ሲኤኤስ(DC CAS) ፈተና ላይ ያሉ ዉጤቶች ጋር በቀጥታ ሊወዳደሩ አይገባቸዉም፡፡የፒኤአርሲሲ(PARCC) ፈተናዎች ተማሪዎች መልሶቻቸዉን እንዲያብራሩ የሚጠይቅ እና በዓለም ዙሪያ ላይ ስራ ላይ የሚዉሉ እዉቀቶችን እና ክህሎቶችን፣የብስለት አስተሳሰብ፣ትንተና፣እና ጽሁፍን የሚለካ ፈተና ነዉ፣ይህ ደግሞ ከዲሲ ሲኤኤስ(DC CAS) ፈተናዎች ለየት ያደርገዋል፡፡ሪፓርቱ ልጅዋ ከእኩዬቹ/ቿ ጋር እርስ/ሷን ተመሳሳይ የሚያደርገዉን/ጋትን ሁኔታ የአሁኑ የተማሪዎች ዉጤትን ካለፋ የዲሲ ሲኤኤስ(DC CAS) ዉጤቶች ጋር ቀጥተኛ ባልሆነ መልኩ በማነጻጸር ያሳያል፡፡

## 5) ቀጥሎ ያለዉ ነገር ምንድን ነዉ?

በዉጤት ሪፓርቱ ላይ ያለዉ መረጃ የተማሪዉን ለዉጥ ለመለካት እና ክህሎቶችን ለመገንባት የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ለመስጠት የተዎቀረ ነዉ፡፡የዉጤት ሪፓርቱ እርስዎ የልጅዎን ዉጤት በተመለከተ አስተማሪዉን ሊጠይቁ የሚችሉዋቸዉን ጥያቄዎች ይዟል፡፡በቀጣዩ ገጽ ላይ፣ልጅዋን ለመርዳት ስለሚያስችሎት ተጨማሪ አቅርቦቶች የበለጠ ያዉቃሉ፣ከዚህም በተጨማሪ በዉጤት ሪፓርቱ ዙሪያ ከልጅዋ እና ከአስተማሪዉ ጋር ለመወያየት የሚጠቅሙ ፍንጮችን ያገኛሉ፡፡

## ስለ ልጅዋ ዉጤት ሪፓርት የበለጠ ማወቅ ይፈልጋሉ?

ስለ ፒኤአርሲሲ(PARCC) ግምገማዋች እና የኮመን ኮር ስቴት ስታንዳርድስ የበለጠ መረጃ ማግኘት ከፈለጉ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ድህረ ገጾች ይጎብኙ፡

- ➢ [OSSE.dc.gov/parcc](OSSE.dc.gov/parcc) በፒኤአርሲሲ(PARCC) ግምገማዋች እና የኮመን ኮር ስቴት ስታንዳርድስ ዉጤት ሪፓርቶቹ ላይ ዲሲ-ላይ ያተኮረ መረጃን ለማግኘት ይጠቀሙት፡፡
- ➢ [PARCConline.org](PARCConline.org) ስለ ግምገማዋቹ እና ለወላጆች እና ተማሪዋች የሚጠቅሙ አቅርቦቶች ላይ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ይጠቀሙት፡፡
- ➢ [CoreStandards.org](CoreStandards.org) ስለ ኮመን ኮር ስቴት ስታንዳርድስ የበለጠ ለማወቅ ይጠቀሙት፡፡

## የልጅዋን የፈተና ዉጤቶች ከደረሱት በሁዋላ፣ቀጣዩ ነገር ምንድን ነዉ?

ግምገማዋቹን በመጠቀም ልጅዋን በትምህርት ዙሪያ ለመርዳት እንዲችሉ የሚያግዙት በቁጥር በዛ ያሉ አቅርቦቶች ይገኛሉ:

- ➢ [GreatSchools.org](GreatSchools.org) በቤት ዉስጥ ትምህርት እና መልመጃዋችን ለማካሄድ የሚረዱ ይዘቶችን እና በክፍል ደረጃ ላይ ያተኮሩ ቪዲዮዋችን ያቀርባል፡፡
- ➢ [BeALearningHero.org](BeALearningHero.org) ለወላጆች የሚጠቅሙ በዛ ያሉ አቅርቦቶች አሉት፣ይህም በክፍል ደረጃ፣የትምህርት ዘርፍ እና ይዘት ላይ በመመርኮዝ አቅርቦቶችን የሚያቀናብር የክህሎት መገንቢያ ገጽ እና የመማሪያ መሳሪያዋች ገጽን ያካትታል፡፡
- ➢ [HomeworkHelpDesk.org](HomeworkHelpDesk.org) የቤት ስራ ጥያቄዋች ላይ ወላጆችን እና ተማሪዎችን መርዳት በሚችሉ አስተማሪዋች የቀጥታ ጥያቄ እና መልስ አገልግሎትን ያቀርባል፡፡
- ➢ [PARCCOnline.org](PARCCOnline.org) ከ 3 እስከ 11 ክፍል ደረጃ ላሉ ተማሪዎች የመለማመጃ ፈተናዋች እና የናሙና ጥያቄዎችን ያቀርባል፡፡

## ስለ እርሱ/ሷ ዉጤት በተመለከተ ልጄን እንዴት ማናገር እችላለሁ?

ወላጆች ልጆቻቸዉን ማነጋገር ላይ ባለሙያ ናቸዉ፡፡ ስለ ልጅዋ የፈተና ዉጤቶች በሚወያዩበት ወቅት ማስታወስ የሚገባዎት ጥቂት ጠቃሚ ነገሮች ከታች ተዘርዝረዋል:

- ➢ የፈተና ዉጤቶች ነጠላ የሆኑ መለኪያዎች ብቻ ናቸዉ፡፡
- ➢ ይህ አዲስ ፈተና ነዉ፣እናም ሁሉም ተማሪዋች እስኪለምዱት ድረስ ጊዜ ይፈልጋል፡፡
- ➢ በጥንካሬዋች ላይ ያተኩሩ፡፡
- ➢ እድገት የሚታይባቸዉ ክፍሎች ላይ የበለጠ ለመስራት የሚረዱ እቅድ ንድፎች ላይ ይወያዩ(ለምሳሌ፣በድህረ ገጽ ልምምዶች፣ከአስተማሪ ጋር አብሮ መስራት)

## የልጄን አስተማሪ ስለ እርሱ/ሷ ዉጤት በተመለከተ እንዴት ማናገር እችላለሁ?

ከልጅዋ አስተማሪ ጋር ለሚያደርጉት ዉይይት የሚረዱ ጥቂት ጥያቄዋች ከታች ተዘርዝረዋል፡፡

- ➢ በዚህ ዓመት በሂሳብ እና በንባብ የትምህርት ዘርፎች የልጄ የትምህርት ግቦች ምንድን ናቸዉ ?
- ➢ በሂሳብ እና በእንግሊዘኛ ቋንቋ ጥበብ የእኔ ልጅ ዉጤት እንዴት ነዉ?
- ➢ እነዚህን ግቦች ለማሳካት በትምህርት ቤት እና በቤት ዉስጥ የሚያስፈልጉ ተጨማሪ ድጋፎች ምንድን ናቸዉ?
- ➢ በእርስዋ እይታ ላይ በመመርኮዝ፣የእኔ ልጅ መልካም ዉጤት ያስመዘገበዉ የትኛዉ የትምህርት ዘርፍ ላይ ነዉ? የእኔ ልጅ እድገት ያሳየባቸዉ ክፍሎቹ ጥቂቶቹ እነማን ናቸዉ?